# የብሕትውና ኑሮ፡- መላእክት በምድር ላይ

## 1.አጀማመር

### 1.1 በሕገ ልቡና

የብሕትውና ኑሮ የተጀመረው ከሰው ልጅ ወደዚህች ምድር መምጣት አንሥቶ ነው፡፡ ደቂቀ ሴት ከቃየል ልጆች ኑሮና ግብር ተለይተው በደብር ቅዱስ በንጽሕና በቅድስና ይኖሩ እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል( ዘፍ.6÷1-3፤ ሄኖክ 2÷1-2)

አባታችን ሄኖክም በዘመኑ ከነበሩት ግብረ ሰዶማውያን ርቆ፣ ሰዎችን ለጥፋት ውኃ ከዳረገው ኃጢአት ተለይቶ፣ ንጹሕ እግዚአብሔር ንጽሕናን ይሻል በማለት በሕገ ልቡና ተመርቶ በእግረ ገነት ለሰባት ዓመታት በብሕትውና ከኖረ በኋላ በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ ከአካለ ሥጋ ወደ ብሔረ ሕያዋን መነጠቁን መጽሐፈ ሄኖክ ያስረዳል፡፡ የመልከ ጼዴቅም የኑሮ ሥርዓት ይህንኑ የባሕታውያን ሕይወት የተከተለ ነበር( ዘፍ.14÷17-24)፡፡

### 1.2 በሕገ ኦሪት

ይህ የብሕትውና ኑሮ ከሕገ ልቡና ወደ ሕገ ኦሪት ተላልፎ አባታችን ኤልያስን የመሰለ መናኝ ለማስገኘት በቅቷል፡፡ የኤልያስንም ሕይወት ደቀ መዝሙሩ ኤልሳዕ ተረክቦታል፡፡

### 1.3 በዘመነ ሐዲስ

ወደ ዘመነ ሐዲስም ስንመጣ የዮሐንስ መጥምቁ ሕይወት የዚህ ተከታይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ የ30 ዓመት ወጣት ሆኖ እስኪገለጥ ድረስ በጨው ባሕር አጠገብ በሚገኘው የቁምራን ገዳም የኖረ ሲሆን በኋላም የግመል ፀጉር ለብሶ የበረሃ አንበጣ እየበላ በሄኖም ሸለቆ በመኖር በዮርዳኖስ ወንዝ ሕዝቡን በንስሐ ጥምቀት ያጠምቃቸው ነበር (ማር.1÷1-11)፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሐዲስ ኪዳኑ ባሕታዊ ስለ መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ ‹‹እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ›› በማለት መስክሮለታል( ዮሐ.5÷35)፡፡

ልዑለ ባሕርይ ኢየሱስ ክርስቶስም በ30 ዘመኑ በፈለገ ዮርዳኖስ በዕደ ዮሐንስ ከተጠመቀ በኋላ ወደ ቆሮንቶስ ገዳም በመግባት የምነናን እና የብሕትውናን ኑሮ አጽንቶ አስተምሮናል፡፡ ዛሬ አሠረ ፍኖቱን የተከተሉት አባቶቻችን እንደሚያደርጉት ሁሉ በነዚያ 40 ቀናት ወደ በረሃ ወርዶ ከአራዊት ጋር ኖረ( ማር.1÷13)፡፡ ከዲያብሎስ ተፈትኖ ድል በማድረግም ድል የምናደርግበትን ኃይል ሰጠን፡፡ መድኃኒታችን

ወደ ፈቃዱ አርአያ ምሳሌ ይሆነን ዘንድ በገዳመ ቆሮንቶስ ዲያብሎስን ድል ባደረገው ጊዜ መላእክት አገለገሉት። በዚህም እኛ እሱን ብንመስለው ዲያብሎስንም ድል ብንነሣው ኑሮአችን ከመላእክት ጋር እንደሚሆን አስተማረን(ማር.1÷13፣ ማቴ 1÷11)።

በአንድ ወቅት ደቀ መዛሙርቱ መድኃኒታችንን ‹‹መጋባት አይጠቅምምን›› ብለው በጠየቁት ጊዜ እንዲህ በሚል ቃል አስተምሯቸው ነበር። «ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም። በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ። ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ። ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው» (ማቴ.19÷10-10)።

ስለ መንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች የተባሉት ሁሉ እያላቸው፣ ሁሉን ማድረግ እየቻሉ ነገር ግን ይህንን ዓለም ንቀው መድኃኒታቸውን መስለው፣ ድምፀ አራዊትን ግርማ ሌሊትን ታግሠው፣ የእሾህ አክሊሉ ምሳሌ የሆነውን ቆብ ደፍተው፣ ምድረ በዳ ወርደው ከአራዊት ጋር እየኖሩ (ማር.1÷13) ከዲያብሎስ ጋር የሚጋደሉት የሃይማኖት አርበኞች ናቸው።

ጃንደረብነት ሦስት ዓይነት መሆኑን ጌታችን ገልጦልናል። በተወለዱ ጊዜ በችግር ምክንያት ጃንደረቦች (ስልቦች) የሆኑ አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በአገራችን አንዳንድ ቦታዎች፣ በመካከለኛውና ደቡባዊው አፍሪካ በአብዛኛው እንደሚታወቀው የማኮላሸት ተግባር የሚፈፀምባቸው አሉ። ሳይፈልጉ በሰዎች አስገዳጅነት የሚሰለቡ እንዳሉ ሁሉ ሥልጣንሽተው ማዕረግ ፈልገው ጃንደረባ የሚሆኑም አሉ።

ሦስተኛዎቹ ግን «ሁሉን ትተህ ተከተለኝ» ያለውን ቃል ሰምተው፣ ያላቸውን ሁሉ ለመንግሥተ ሰማያት ጌታ ለቅዱስ እግዚአብሔር ሲሉ ርግፍ አድርገው የተከተሉት፤ ከዚህ ዓለም ግብር ርቀው የዘወትር ሥራቸው ጸሎትና መዝሙር፤ ቅዳሴና ስግደት የሆነ ምድራውያን መላእክት ናቸው። ጌታችን ይህንን ጉዳይ ለሀብታሙ ጎልማሳ ጥያቄ በሰጠው መልስ ላይ አጠናክሮ አብራርቶ አስተምሮናል።

ባለጸጋው ‹‹የዘላለምን ሕይወት እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ?›› ብሎ በጠየቀው ጊዜ ጌታ «ትእዛዛትን ጠብቅ» በማለት የወጣንያንን ትምህርት አስተማረው። ጎልማሳው ግን ‹‹ይህን ሁሉማ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ ደግሞስ የሚጐድለኝ ምንድነው?›› በማለት ጠለቅ ብሎ ጠየቀ። በዚህ ጊዜ ‹‹ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሽጠህ ለድኾች ስጥና ተከተለኝ›› ሲል አስተማረው። ጐልማሳው ግን ይህን መሸከም አቅቶት ለንብረቱ ሳስቶ እያዘነ ሄደ (ማቴ.19፣16-212)። ለዚህ ነበር ጌታችን ‹‹ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው›› በማለት ያስተማረው።

አባቶቻችን መነኮሳትና ባሕታውያን በረሃ የወረዱት፣ሁሉን ሸጠው፣ለድኾች መጽውተው የመነኑት ይህንን ጌታ ለፍፁማን የሰጠውን ትምህርት መሠረት አድርገው ነው፡፡

**1.4 በመጀመርያዎቹ ክርስቲያኖች**

ይህ ኑሮ በመጀመሪያው መ/ክ/ዘመን በነበሩ ክርስቲያኖች ዘንድ የተለመደ እንደነበር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን በላከው መልእክቱ ፍንጭ ሰጥቶናል፡፡ ‹‹ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፡፡ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፣ በዋሻና በምድር ጉድጓድ (ግበበ ምድር) ተቅበዘበዙ›› ሲል (ዕብ 11÷37)፡፡ ዛሬም በየበረሃው የፍየል ሌጦ ለብሰው አበው የሚጋደሉት የእነዚህን ክርስቲያኖች አርአያ አንሥተው ነው፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የትዳርን ነገር በተናገረበት አንቀጹ «ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁ፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው፡፡ አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ» በማለት የክርስቲያኖች የኑሮ ሥርዓት ሁለት ዓይነት መሆኑን አስተምሮናል (1ቆሮ.7÷7)፡፡ እነዚህም የትዳር እና የብሕትውና (ምንኩስና) ሕይወት ናቸው፡፡ የብሕትውና (ምንኩስና) ኑሮ ከጥንት ከዘመነ አበው ጀምሮ የመጣ፣ ጌታችን ያጸናው፣ ሐዋርያት የሰበኩት መጽሐፍ ቅዱስዊ ትምህርት እንጂ «ብዙ ተባዙ» ከሚለው አንቀጽ ጋር የሚጋጭ ሰው ሠራሽ ሥርዓት አይደለም፡፡

**2. የሥርዓተ ምንኩስና ታሪክ**

**2.1 አባ ጳውሊ እና አባ እንጦንስ**

**2.1.1 አባ ጳውሊ**

በተባሕትዎ መኖር ከጥንት ዘመን የመጣ ይሁን እንጂ የብሕትውናን ኑሮ ሥርዓት በወጣለት መልኩ የጀመረው አባ ጳውሊ የተባለው ግብፃዊ አባት ነው፡፡ በንጉሥ ዳክዮስ ዘመነ መንግሥት በክርስቲያኖች ላይ በተነሣው ስደት ምክንያት አባ ጳውሊና ቀይቶም ደግሞ ሌሎች የአካባቢው ክርስቲያኖች በግብፅ በረሃዎች ውስጥ በምናኔ ይኖሩ ነበር፡፡

ይህንን አባ ጳውሊ የጀመረውን ሥርዓት አጠናክሮ ለማስፋፋት ያበቃው ደግሞ አባታችን አባ እጦንስ ነው (251-356 ዓ.ም.)፡፡

### 2.1.2 አባ እንጦንስ

አባ እንጦንስ ግብፅ ውስጥ ቆማ በተባለች መንደር ከሀብታም ቤተሰቦች በ251 ዓ.ም ተወለደ። ወዳጆቹ ገና የ20 ዓመት ወጣት እያለ ስላረፉ በማቴ.19÷21 ላይ ያለውን ትምህርት መሠረት አድርጎ የወረሰውን ሀብት በሙሉ በመሸጥ ለድኾች አከፋፈለና ወደ ግብፅ በረሃ በመውረድ ለ85 ዓመት በተጋድሎ ኖሯል።

የአባ እንጦንስ ዓላማ ከሰው ርቆ በብሕትውና በበረሃ ለመኖር ነበር። ነገር ግን ተአምራቱን የሰማው ሕዝብ ከግብፅ ብቻ ሳይሆን ከመካከለኛው ምሥራቅና ከአውሮፖ ምድር ሳይቀር ወደ በአቱ ይጐርፍ ጀመር። በኋላም በሕይወቱ የተማረኩ ባሕታውያን በዙሪያው ባሉ ዋሻዎች መኖር ጀመሩ።

የአባ እንጦንስን የሕይወት ታሪክ የጻፈለት አባታችን አትናቴዎስ ሲሆን አትናቴዎስም ሥርዓተ ምንኩስናን የተቀበለው ከዚሁ አባት ነው። ታላቁ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስም ዝናውን በመስማቱ «በጸሎትህ አስበኝ» በማለት ደብዳቤ ጽፎለት እንደነበር ታሪኩ ይናገራል።

አባ እንጦንስ ለ85 ዓመታት በብሕትውና ሲኖር ከበኣቱ የወጣው ሁለት ጊዜ ብቻ ነበር። የመጀመሪያው በንጉሥ መክስምያኖስ ትእዛዝ ስደትና መከራ የደረሰባቸውን ክርስቲያኖችን ለማጸናናት በመላዋ ግብፅ በ311 ዓ.ም. ያደረገው ጉዞ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አርዮሳውያን በቅዱስ አትናቴዎስ ላይ በተነሡበት ጊዜ ለመንፈስ አባቱ ለሐዋርያዊው አትናቴዎስና ለንጽሕት ተዋሕዶ እምነቱ ያለውን ቆራጥነት በመግለጥ ሕዝቡን ለማጽናናት በ338 ዓ.ም ደቀ መዛሙርቱን አስከትሎ የተጓዘው ሐዋርያዊ ጉዞ ነው።

የባሕታውያኑ በአባ እንጦንስ ዙሪያ መሰባሰብ ለማኅበር ጸሎት፣ ከዘራፊዎች ለመጠበቅና የደከሙ አበውን ለመርዳት አስችሏቸዋል። በዚህም የመጀመሪያው የገዳማውያን የማኅበር ኑሮ ተጀመረ።

አባ እንጦንስ የመነኮሳቱ ልብስ ነጭ ፈረጅያና ቆብ፣ መታጠቂያቸውም ከቆዳ የተሠራና ሠቅ እንዲሆን ወስኖ ነበር።

መነኮሳቱ ሳምንቱን በየበኣታቸው ሲጸሙና ሲጸልዩ ሰንብተው እስከ እሑድ ምሽት ድረስ ደግሞ በአባ እንጦንስ ዋሻ ዙሪያ ተሰባስበው ሲጸልዩና ሥረዓተ አምልኮ ሲፈጽሙ ይውሉ ነበር። አባ እንጦንስ በዚህ ሁኔታ ሥርዓተ ምንኩስናን አስፋፍቶ በተወለደ በ105 ዓመቱ ዐርፎአል።አባ ጳውሊ የጀመረውን ሥርዓተ ምንኩስና አጠናክሮ ያስፋፋው አባ እንጦንስ ነው።

**2.2 አባ ጳኩሚስ**

በሥርዓተ ምንኵስና ታሪክ ሌላውን ታላቅ ሥፍራ የያዘው ደግሞ የአባ እንጦንስ ደቀ መዝሙር የነበረው አባ ጳኩሚስ ነው (230-346 ዓ.ም.)፡፡ አባ ጳኩሚስ ግብፅ ውስጥ ኤስና በምትባል መንደር ከአረማውያን ቤተሰቦች በ290 ዓ.ም. ተወለደ፡፡ በቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት ለውትድርናም ተመልምሎ አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ በውትድርናው ዘመን የክርስቲያኖችን ቆራጥነት፣ደግነትና ርኅራኄ በማየቱ ልቡ ስለተነካ ግዳጁን ፈጽሞ ሲመለስ በ313 ዓ.ም. የክርስትናን እምነት ጠንቅቆ በመማር አምኖ ተጠመቀ፡፡

የአባ ጳኩሚስ ልቡና የቅዱስ እንጦንስ ደቀ መዝሙር በነበረው በአባ ጴላጦንስ ኑሮ ስለተማረከ ወደ በረሃ ወርዶ የብሕትውናን ኑሮና ሥርዓት ሲማር ከቆየ በኋላ በ320 ዓ.ም. በዓባይ ወንዝ አጠገብ ታቤኒስ ከተባለው ቦታ የራሱን ገዳም መሠረተ፡፡ በዙሪያው ለተሰበሰቡት መነኰሳትም የአንድነት ኑሮ ሕግ አወጣላቸው፡፡ በአባ እንጦንስ ለተጀመረው የማኅበረ መነኰሳት ኑሮ የተጠናከረ ሥርዓት አውጥቶ የበለጠ ከማስፋፋቱም በተጨማሪ ዘጠኝ የወንድና 2 የሴቶች ገዳማት መሥርቷል፡፡

አባ ጳኩሚስ ያወጣው የመነኰሳት የአኗኗር ሕግ ዋናው ቅጂ ሲጠፋ ወደ ላቲን የተተረጐመው ግን እስከዛሬ ድረስ ይገኛል፡፡ ከሕግጋቱ መካከል፡-

- መነኮሳት ጠዋትና ማታ በማኅበር እንዲጸልዩ፣
- በኅብረት በአንድነት እንዲሠሩ፣
- ቅዱሳት መጻሕፍትን አዘውትረው እንዲመለከቱ፣
- የቁም ጽሕፈት እንዲማሩ፣
- ገቢና ወጪአቸው አንድ ላይ እንዲሆን፣
- በአንድነት እንዲመገቡ፣
- አንድ ዓይነት ልብስ እንዲኖራቸው፣
- ንጽሕ ጠብቀው እንዲኖሩ፣
- ደግነት፣ ፍቅርና ታዛዥነት እንዲኖራቸው፣የሚሉት ይገኙበታል፡፡

አንድ ሰው ወደ ገዳማቱ ሲመጣ የሦስት ዓመት አመክሮ ይሰጠውና ጠባዩና ፍላጐቱ ይገመገማል፡፡ ከዚያ በኋላም ብርታቱና ጽናቱ ታይቶ ወደ ማኅበረ መነኰሳቱ ይቀላቀላል፡፡ አባ ጳኩሚስ በዚሁ ዓይነት መንገድ ሥርዓት ሠርቶ ሕግ አጽንቶ ገዳማትን ካስፋፋ በኋላ በተወለደ በ56 ዓመቱ በ346 ዓ.ም. ዐረፈ፡፡

## 3. ሥርዓተ ምንኩስናን በሌላው ዓለም ያስፋፉ አበው

### 3.1 አትናቴዎስ ሐዋርያዊው (295-373 ዓ.ም.)

ቅዱስ አትናቴዎስ ከታላቁ ርዕሰ ገዳማውያን ከአባ እንጦንስ ዘንድ ሥርዓተ ምንኩስናን ተምሮ ፈጽሟል፡፡ የአባ እንጦንስን የሕይወት ታሪክ (ገድል) የጻፈውም እርሱ ነው፡፡ አርዮሳውያን በቅዱስ አትናቴዎስ ላይ በግፍ በተነሡበት ጊዜ ወደ ሮም በመሰደድ ከ339-346 ዓ.ም. ተቀምጧል፡፡ የሮም ክርስቲያኖች አትናቴዎስና ተከታዮቹ የለበሱትን የመነኰሳት ልብስና ቆብ ተመልክተው ተገረሙ፡፡ እርሱም በቆየባቸው ሰባት ዓመታት ከአባ እንጦንስ የተማረውን የመነኰሳት ሕግና አኗኗር አስተምሯቸዋል፡፡ በሮማ ምድርም ሥርዓተ ምንኩስናን ለማስፋፋት የመጀመሪያው አባት አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ነው፡፡

### 3.2 ቅዱስ ባስልዮስ ታላቁ (330-379 ዓ. ም)

ባስልዮስ በግብፅ ገዳማት በብሕትውና ከቆየ በኋላ ከ360 ዓ.ም. ጀምሮ በታናሽ እስያ (ዛሬ ቱርክ በሚባለው አካባቢ) የምነናን ኑሮ በመመሥረት ዛሬ የግሪክ፣ ሩሲያ፣ ወዘተ. አብያተ ክርስቲያናት የሚገለገሉበትን የመነኰሳት ሕግ ያወጣው እርሱ ነው፡፡

### 3.3 ዮሐንስ ካስያን (360-435 ዓ.ም.)

ግብፅ ውስጥ በቴብያድና ጥቂት ዓመታት በብሕትውና ከቆየ በኋላ ወደ ፈረንሳይ በመመለስ በ415 ዓ.ም. በፈረንሳይ ማርሴይ አጠገብ ሁለት ገዳማትን መሠረተ፡፡ በግብፅ ያጠናውን ሥርዓተ መነኰሳት መሠረት አድርጐ ሁለት መጻሕፍትንም አዘጋጅቷል፡፡

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ በአባ ጳውሊ የተጀመረው የምንኩስና ሕይወት በመላው ዓለም ሊስፋፋና ወደሀገራችንም ለመድረስ በቅቷል፡፡ የመጀመሪያውን የሴቶች ገዳም የመሠረተችው ደግሞ የአባ ጳኩሚስ እኅት ማርያም ነች፡፡